# የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ከኢትዮጵያ ቢነሳስ?

መለስ ዓ.

ኒውዮርክ የዓለም የፋይናንስና የዲፕሎማቲክ ማዕከል ናት፡፡ጄኔቭ በበኩሏ የዓለም የህግና ሰብዓዊ መብት ጉዳይ መቀመጫ እንደሆነች ይነገራል፡፡ ወደ አህጉራችን አፍሪካ ስንመጣ ናይሮቢ ብዛት ያላቸው የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ማዕከል እንደሆነች የሚታወቅ ሲሆን፣ አዲስ አበባም የአፍሪካ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ማዕከል ናት ቢባል ክርክር ውስጥ የሚገባ ወገን እምብዛም አይኖርም፡፡ ሁሉም አገሮች ይህን አይነቱን ዕድል ለሌላ ወገን አሳልፈው እንዲሰጡ የሚያስገድድ ውስጣዊና ውጪያዊ ሁኔታዎችን ለመከላከል ቢሞክሩም ፈተናው ለአንዳንዶቹ ቀላል አይደለም፡፡የውጭ ግንኙነት ም/ቤት የተባለ የጥናትና ምርምር ተቋም ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተነበየው ኒውዮርክ የዓለም የፋይናንስ ማዕከልነቷን ልትነጠቅ የምትችልበት አደጋ ከፊት ለፊቷ መጋረጡን ነው፡፡ የአሜሪካ ሴኔትና የከተማዋ አስተዳደር ግሌን ሁበርድና ጆን ኤል ቶሮንቶ የተባሉ ኢኮኖሚስቶች የሚመሩትን አጥኚ ቡድን በማቋቋም ይህን አደጋ ለማስቀረት መፍትሄ ማፈላለግ ይዟል፡፡ አገራችን ከኒውዮርክ ልትማረው የሚገባ ጉዳይ ያለ ይመስለኛል፡፡ አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ ሆና ዝንተ-ዓለም ለመቀጠሏ ምን ዋስትና አለን? ቀደም ሲል የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አሁን ደግሞ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ እንድትሆን ቢወሰንም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተቋጨ አጀንዳ አይመስልም፡፡ ይሁን እንጂ ከመንግስት የተጠናጠል ጥረት ውጭ እንደ አንድ ሰው ሆነን በመንቀሳቀስ አደጋውን ለማስቀረት ስንንቀሳቀስም አይታይም፡፡

የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ ከሰሞኑ ካምፓላ ውስጥ ሲካሄድ የህብረቱ አዲስ አበባ መቀመጫነት ተነስቶ ውይይት ሲካሄድ እንደነበር ዴይሊ ሞኒተር የተባለ የዩጋንዳ ጋዜጣ ዘግቧል፡፡ ፎርቹን የተባለ ሳምንታዊ ጋዜጣ ሐምሌ 25/2002 እንዳመለከተው ሊቢያ ሐምሌ ወር ላይ በዙር የሚካሄደውን ስብሰባ በቋሚነት ማስተናገድ እንድትችል ጥያቄ አቅርባለች፡፡ እነዚህ ዘገባዎች አገራችን የህብረቱ መቀመጫ ከአዲስ አበባ እንዳይነሳ ምን አይነት የአጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አለን የሚል ጥያቄ የሚጭር ነው፡፡ ፀሀፊው የመረጠው ርዕስ አሸባሪ (Alarmist) እንደሆነ ይገነዘባል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ፅሁፍ ሲያዘጋጅ ጥያቄውን በተመሳሳይ መልኩ ለተለያዩ ሰዎች አቅርቦ ያገኘ ው ምላሽ ድንጋጤ የተሞላባቸው ነበሩ፡፡ ፀሃፊውም ይህን ስሜት ይጋራል፡፡ የተሰጡት ምላሾች ኢትዮጵያውያን ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዛሬም ከአፍሪካ ህብረት ጋር ጥብቅ ቁርኝት (Sentimental Attachment) እንዳለን እንዲገነዘብ አድርጎታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ቁርኝት ብቻውን በቂ አይመስለኝም፡፡የሰይጣን ጆሮ አይስማ ማለት ብቻውን አያስኬድም፡፡

ጽ/ቤቱን በአገራችን ጠብቆ የማቆየት ጥያቄ የመንግስት አሊያም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊነት ብቻ መሆን ይገባዋል? የንግዱ ማህበረሰብ ምሁራንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የመገናኛ ብዙሃን በጠቅላላ ህብረተሰቡ የየራሱ ሚና እንዳለው ግንዛቤ አለው? ይህ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል።

<u>አዲስ አበባ አፍሪካዊቷ ብራስልስ</u>

የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ከአገራችን ተነስቶ ሌላ አገር እንዲሆን በተለያዩ መድረኮችና አጋጣሚዎች ሁሉ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማቅረብ የተለመደ ከሆነ ቆይቷል። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ለቀረበ ተመሳሳይ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ሁሌም የሚታወስ ነው። የአቶ መለስ አስተያየት "በኢትዮጵያ መንግስታት ቢለዋወጡም እንኳን አፍሪካውያንና አፍሪካን በተመለከተ የአገራችን አቋም የማይናወጥና የርዕዮተ-ዓለም ድንበርን የተሻገረ ነው። አንጋፋውን የደቡብ አፍሪካ የነፃነት መሪ ኒልሰን ማንዴላ(ማዲባ) ማን አሰለጠናቸው? ለአፍሪካ ነፃነት ከኢትዮጵያ የበለተ አስተዋፅኦ አለኝ የሚል አፍሪካዊ አገር ካለእጁን ያውጣ" ነበር ያሉት። በኮልፌ የፖሊስ ማሰልጠኛ መሰረታዊ ወታደራዊ ትምህርት ሀ ሁ የቀሰሙት ማንዴላ የመጀመሪያውን ሽጉጥ ያገኙ ት ከጄኔራል ታደሰ ብሩ እንደሆነ የማንዴላን ረጅም የህይወት ውጣ ውረድ በሚዳስሰው የህይወት ታሪካቸው በግልፅ አስቀምጠውታል። አፄ ኃይለስላሴም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሰረት ካደረጉት ጥረት በተጨማሪ ድህረ ቅኝ አገዛዝ ቢያፍራን ጨምሮ በተለያዩ አገሮች ውስጥ የተከሰቱ ውዝግቦች በሰላማዊ መንገድ እልባት እንዲያገኙ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እንዳሉት የደርግ መንግስት በአገር ውስጥ ካለው የከፋ ስም ውጭ ዚምባቡዌ፣ ናሚቢያና ደቡብ አፍሪካ ነፃ እንዲወጡ አስተዋፅኦ አድርጓል። ይህ ድጋፍ የቀድሞው ፕሬዚዳንት የግል ድጋፍ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ እንደአገር ለሌሎች አፍሪካውያን ነፃነት ዕውን መሆን ያላትን ቀናዒነት ያሳየችበት እንደሆነ ቀድሞ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ኃ/ማሪያምን ህይወት በዳሰሰው ቁጥር ሁለት መፅሃፍ ላይ ተመልክቷል።

ሶፊያ ግሩብ የተባሉ ፀኃፊ እንደሚሉት አዲስ አበባ የአፍሪካ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ መዲና ናት:: ፀኃፊዋ ርዕሰ መዲናችንን የአውሮፓ ህብረት፣ የኔቶ እና ሌሎች የአውሮፓ ህብረት መቀመጫ ከሆነችው ብራስልስ ጋር አመሳስለዋታል:: ከብራስልስ ከህብረቱ ውጭ የአውሮፓ ፓርላማ፣ የህብረቱ ሚኒስትሮች ም/ቤት፣ የአውሮፓ ኮሚሽን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኮሚቴ ጽ/ቤቶች መቀመጫ ናት:: 450 ሚሊዮን ለሚሆነው የአውሮፓ ነዋሪ ብራስልስ ዋና ከተማ በመሆኗ ከኒውዮርክ ቀጥላ 3800 ዲፕሎማቶች የተወከሉባት፣ 1400 የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና 1000 የሚሆኑ የመገናኛ ብዙኃን መናኸሪያ ናት::ብራስልስ በዚህ ትሩፋቷ ምክንያት በአውሮፓ ህብረት አገሮች ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላት ከተማ እንድትሆን አስችሏታል:: ይህንን አስጠብቆ ለማቆየት የቤልጂየም መንግስት ከተማዋ ለዲፕሎማቶች የተመቸች ከተማ ሆና እንድትቀጥል የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል:: ሁሉም አውሮፓዊ ከቤቱ ቢርቅም ብራስልስ ውስጥ ሲገኝ እንደ ቤቱ እንዲሰማው ይሞክራል::

ሶፊያ ግሩብ የተባሉት ፀኃፊ እንደሚናገሩት እንደተላንቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሁሉ የአፍሪካ ህብረትን መቀመጫ ከአገራችን ለመውሰድ አንዳንዶች አቆብቁበው ይሰራሉ:: ከእነዚህም ሴኔጋል አንደኛዋ እንደነበረች የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው :: የአፍሪካ አንድነት መቀመጫ አክራ እንዲሆን ጋና የቀድሞውን የአገሪቱ መሥራች አባት ከዋሚ ንክሩማ ስምና ገናናነት ተገን በማድርገ የድርጅቱን ፅ/ቤት ለመውሰድ እንደሞከረች ፀኃፊዋ ያስታውሳሉ:: ደቡብ አፍሪካም ቢሆን የአህጉሪቱ የኢኮኖሚ ሞተር ከመሆኗ አንፃር የህብረቱ ጽ/ቤት ወደ አገሯ ቢዞር አትጠላም :: የሊቢያው መሪ ወንድም ሙዐመር ጋዳፊ ጽ/ቤቱን ወደ ትውልድ መንደራቸው ስርጥ ለመውሰድ ለአፍሪካ መሪዎች ቪላ ቢገነቡ፣ በእጅ ቢሉ ሊገርመን አይገባም :: ነገ ከነገ ወዲያ ሊቢያ አይደለም ከናይጄሪያ እስከ ኤርትራ ብሎም አንጎላ ጽ/ቤቱ ይገባናል የሚል ሙግት ቢገጥሙ ጤናም የላቸውም ወይ? ልንል አይገባም :: ዋናው ጉዳይ የአፍሪካ ህብረት ጽ/ቤት በኢትዮጵያ እንዲሆን አገራችን ለጥቁር ህዝቦችና አፍሪካውያን ነፃነት ያደረገችው አስተዋፅኦ በገንዘብ የሚለካ ባይሆንም ይኸኛው ትውልድ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራት አሉ :: በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ውስጥ የተከበሩ አቶ ክፍሌ ወዳጆ እና አቶ ከተማ ይፍሩ እንዲሁም በህብረቱ ውስጥ ደግሞ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ፈለግ ሊከተል የሚችል ትውልድ የግድ ይላል ::

አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት፣ 30 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ዋና ተቋማት፣ ከ100 በላይ የዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች 107 ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች መቀመጫ ናት :: ከኒውዮርክ፣ ብራስልስ እና ጄኔቫ በኋላ ለኢትዮጵያና

የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውክልና ያላቸው ዲፕሎማቶች መቀመጫ በመሆናት። የህብረቱ መቀመጫ እዚህ መሆን ከተምሳሌታዊነት(Symbolism) የዘለለ ትርጉም አለው። እነዚህ ተቋማት አገራችን ውስጥ በመሆናቸው በተፈጠረው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎችና ቤተሰቦቻቸው አያሌ ናቸው ። ስታትስቲካዊ መረጃ ለማግኘት ያደረኩት ጥረት ባይሳካልኝም ሰፊ የታክስ ገቢ ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ እገምታለሁ ። የዓለም አቀፍ ግንኙነት ተቋም እንደጠቀሰው ትላልቅ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ የሆኑ አገሮች ካልሆኑት ይልቅ ፖለቲካዊ ተፅእኖ የማሳረፍ ዕድል አላቸው ። አዲስ አበባ እነዚህ ተቋሞች ጽ/ቤቶቻቸውን ቢያዞሩ ሊታጣ የምትችለውን ጥቅም መገንዘብና ለዚህ የሚመጥን የተግባር እንቅስቃሴ ከሁሉም ወገን ይጠበቃል ። አሜሪካኖቹ ኒውዮርክ የዓለም የፋይናንስ ተቋማት ዘውዷን በለንደን ልትቀማ ትችላለች የሚለው መላምት አስደንግጧቸዋል ። የህብረቱና ሌሎች አህጉራዊና አገር አቀፍ ድርጅቶች በኢትዮጵያ የሚኖራቸው ዘላቂነት የዘላለም አይደለምና የዛኑ ያህል አሳስቦን ልንጨነቅበት ይገባል።

## <u>*ሁሉም መንገዶች ወደ ኒዮርክ ይወስዳሉ* !!</u>

*ታዋቂው አሜሪካዊ ፀሃፊ ኤ.ኤል ዶክትሮው የኒውዮርክ ሙዚየም እ.ኤ.አ.* **1999** *ባሳተመው መፅሃፍ ላይ በፃፈው መግቢያ ''ኒውዮርክ የሕትመት ተቋማት፣ የኮሙኒኬሽን፣ የቲያትር፣ የስነጥበብ ወደብ ናት ። ኒውዮርክ በጡረታ ዘመናቸው የህይወት ትዝታቸውን አረፍ ብለው መፃፍ ከሚፈልጉ የአገር መሪዎች እስከ ለፈጣሪው በፅሞና ፀሎቱን የሚያደርግ ተራ ግለሰብ ድረስ መኖሪያው ናት'' ብለው ፅፈዋል ። ከእ.ኤ.አ.* **1880***ዎቹ ጀምሮ የተለያዩ አገር ዜጎች ወደ ኒውዮርክ መምጣት በመጀመራቸው በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው ነዋሪ የሌላ አገር ዝርያ ያለው አሜሪካዊ ነው ። ከአስር ዓመት በፊት የተካሄደው የህዝብ ቆጠራ እንደሚያመለክተው ስምንት ሚሊዮን ከሚሆነው ነዋሪ ውስጥ እንግሊዘኛ የሚናገረው* **49** *ከመቶ ብቻ ነው ። በዚህም ሳቢያ ሁሉም መንገድ ወደከተማዋ እንደሚወስድ መናገር የተለመደ ነው ።*

*ኒውዮርክ ከዚህ ሃብቷ በተጨማሪ የተለያዩ የቢዝነስ ዘርፎችን፣ የክሬዲት ካርድ፣ ኢንሹራንስ ማዕከላት ይንቀሳቀሱባታል። ታላቁ የዎል ስትሪት የፋይናንስ ባንክ መቀመጫ መሆኗን ሳስተዋለ ከተማዋ የዓለም የፋይናንስ አገልግሎት የስምሪት ማዕከል ናት ቢባል አይበዛባትም ። በዚህ ሃብቷ ከተማዋ ብቻም ሳትሆን አሜሪካ ታላቅ ጥቅም*

ታገኛለች፡፡ የኒውዮርክ ከተማ አጠቃላይ የምርት መጠን (GDP) ውስጥ አስራ አምስት በመቶ፣ አንድ ሶስተኛ የታክስ ገቢዋን ደግሞ የምታገኘው ከፋይናንስ ሴክተር ነው፡፡ ይህ ዘርፍ በከተማዋ ውስጥ ከሚፈጠሩ ዘጠኝ የሥራ እድሎች ውስጥ አንዱን እንደሚፈጥር የውጭ ግንኙነት ም/ቤት ድረ-ገፅ ይጠቅሳል፡፡ በአገር ደረጃም አሜሪካ ከፋይናንስ ሴክተሩ 51 ትሪሊየን፣ አውሮፓ 38፣ ጃፓን 20፣ ምስራቅ ኤዢያ 13 ትሪሊየን ዶላር ያገኛሉ፡፡ ይህም ለአሜሪካ ሰፊ የፋይናንስ አቅም ይፈጥራል ፡፡ ዘ-ኢኮኖሚስት መፅሔት አንዳንድ የግል የፋይናንስ ተቋማትን ጠቅሶ ይፋ እንዳደረገው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኒውዮርክ አይበገሬነት ፈተና ገጥሞታል ፡፡ በአሁኑ ወቅት ከኒውዮርክ ይልቅ ለንደን በተለያዩ የፋይናንስ ሴክተሮች የበላይነቷን እያሳየች ነው፡፡ ይህን ሽግግር የተመለከቱ የፋይናንስ ዘርፍ ተንታኞች እንደሚሉት በሚቀጥለው አስር ዓመት ለንደን የበላይነቷን ታረጋግጣለች፡፡ ይህ ጉዳይ ያሳሰበው የአሜሪካ ሴኔት እና የከተማዋ ም/ቤት አንድ ኮሚቴ በማቋቋም የአደጋውን መንስዔ በማጣራት የመፍትሔ አማራጮችን አቅርቧል፡፡ የኒውዮርክ ከተማ ከንቲባ ማይክል ብሉምበርግ የፋይናንስ ድርጅቶቹ ከአሜሪካ የፋይናንስ ተቋማት የሚገጥማቸው ተደራራቢ እና የተንዛዛ የቁጥጥር ሥራ ሳቢያ(Over Regulation) ወደ ለንደን ለመሸሽ ይገደዳሉ፡፡ ብሉምበርግ እንደሚሉት የፋይናንስ ተቋማቱ በአሜሪካ ከአስር በላይ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ቁጥጥር ሲደረግባቸው በእንግሊዝ በአንድ ብቻ በመሆኑ 15 ዕጥፍ ለማይገባ ወጪ ይዳረጋሉ፡፡

በአሰራር ላይ ከሚስተዋለው አገልግሎት አሰጣጥ ችግር በተጨማሪ ለንደን የተሻለ የቴክኖሎጂ የበላይነት ስላላትና ግሎባላይዜሽን የፈጠሩላትን ዕድሎች በሚገባ በመጠቀሟ ቀጣዩ ዘመን የእሷ እንዲሆን እድል ፈጥሮላታል፡፡ ይሁን እንጂ ኒውዮርክ ዘውዷን አሳልፋ ላለመስጠት ለንደንም አሸናፊነቷን ለማረጋገጥ ከመጣር አልቦዘኑም፡፡ ሁለቱም ልዩ የሚያደርጋቸውን ገፅታዎች ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ለዓለም ያስተዋውቃሉ፡፡ ኒውዮርክ የኒውዮርክ ማራቶን፣ ሃሎዊን ፌስቲቫል፣ ለንደን ደግሞ የለንደን ማራቶን የባሌ እና ኦፔራ ዳንስ አገር፣ የዊምበልደን የሜዳ ቴኒስ ማወዳደርያ እንደሆኑ በማሳየት መልካም ገፅታቸውን ይገነባሉ፡፡ እኛስ ? የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ከአዲስ አበባ መውሰዱን ሞቅ ቀዝቀዝ እያለ የሚካሄድብንን ዘመቻ በመንግስት በሳልና ብርቱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ምክንያት መመከት ቢቻልም ጽ/ቤቱን እዚህ አገራችን ለማቆየት የተደረገው ጥረት በቂ መስሎ አይታየኝም ፡፡ በአፍሪካ አገሮች ስም መንገድ መሰየም አንድ በጎ ጅምር ነው፡፡ የአፍሪካ አገሮች አገራችን ውስጥ የሚገኙ ኤምባሲዎቻቸውን ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዲያሸጋግሩ መሬት መስጠቱም አዲስ አበባ የአፍሪካውያን ከተማነቷን ከቃላት በዘለለ ለማረጋገጥ ይረዳል ፡፡ ሁሉም የአፍሪካ የዲፕሎማሲ መንገዶች ወደአገራችን እንዲያመሩ ግን ከዚህ የበለጠ መስራት ግድ ይላል ፡፡

በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ እና አገራዊ ደህንነት ስትራቴጂ ሰነድ ላይ እንደተጠቀሰው ይህም የውጭ ጉዳይ ዘርፍ አካል በመሆኑ በሚካሄደው እንቅስቃሴ የላቀ አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚችሉትን ወገኖች ማሳተፍና ማስተባበር ይገባል ፡፡

<u>ዘመቻ ጋዳፊ</u>

ጂን ፒየር ማኒጎፍ የተባሉ አጥኚ ኢትዮጵያ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ መዲና ብቻም ሳትሆን የአህጉሪቱ የባህልና ቱሪዝም መናኽሪያ እንደሆነች ያስረዳሉ ፡፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ አፍሪካ እንደ ኢትዮጵያ የተፈጥሮና ታሪካዊ የቱሪስት መስህቦችን የታደለ አገር የለም ፡፡ ለአብነት ግብፅ ፒራሚድ ቢኖራት በዱር እንስሳት አራዊትና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች የታደለች አይደለችም ፡፡ ኬንያንም ብንወስድ በዱር አራዊት ሃብቷ ትመካ እንጂ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ጎንደር፣ ሀረር፣ ሶፍዑመርና የመሳሰሉ ሌሎች ታሪካዊ ቅርሶች ድሃ ናት ፡፡ በኮሮኔል ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ምርምርና ጥናት ተቋም ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሪም ኢትዮጵያ የጥንታዊ የሰው ልጆች መገኛ መሆኗ በአፍሪካ ውስጥ ልዩ ስፍራ እንዲኖራት ያስችላታል ሲሉ ጽፈዋል፡፡ ሁለቱም ምሁራን ኢትዮጵያ እነዚህን እሴቶች በሚገባ በማስተዋወቅ የተሻለ የገፅታ ግንባታ ሥራ በማከናወን በአፍሪካ ውስጥ ያላትን ተደማጭነት ያበልጥ ማጉላት ትችላለች ይላሉ ፡፡ ይሁን እንጂ የሩቆቹን ትተን አዲስ አበባና በዙሪያዋ ያሉ ሙዚየሞች፣ ጋላሪዎች፣ ትክል ድንጋዮች ወዘተ ምን ያህል እናውቃቸዋለን? አትሌቶቻችን ከሚያስመዘግቡት ድል በመለስ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ መሣሪያ እና ብሔራዊ መገለጫ(National Brand) የብራዚሎችን እግር ኳስ፣ የሩሲያዎችን ጂምናስቲክ፣የአሜሪካኖችን አትሌቲክስ ያህል አልተጠቀምንበትም፡፡ ስፖርት በዓለም አቀፉ የገፅታ ግንባታ ረገድ ያለውን ጥቅም ጋና በደቡብ አፍሪካ የዓለም ዋንጫ ላይ በግልፅ አሳይታለች፡፡ ሁሉም አፍሪካዊ ጋናዊ የሆነ እስኪመስለው ድረስ በጋና ሽንፈት ሲቆጭ ነበር፡፡ የናይጄሪያው ፕሬዝዳንት ጆናታን ጉድላክ፣ የፈረንሳዩ አቻቸው ኒኮላስ ሳርኮዚ የእግር ኳስ ብሔራዊ ቡድናቸው ክፉኛ ሽንፈትን ሲጎነጭ እርምጃ ለመውሰድ የተገደዱት ስፖርት በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲው መስክና አገራዊ ክብር ላይ ያለውን እንድምታ ስለሚገነዘቡ ነው፡፡

ከካምፓላ የአፍሪካ የመሪዎች የሰሞኑ ስብሰባ በኋላ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እንደዘገቡት ጋዳፊ የህብረቱን ጽ/ቤት በተመለከተ የሳህል እና ከሳህራ በታች ያሉ አፍሪካ አገሮች ማህበረሰብ (ሴንሳድ) አባል አገራትን በስብሰባው ዋዜማ በማደራጀት ተንቀሳቅሰዋል ፡፡ ይህ ማህበረሰብ ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ሶማሊያና ጂቡቲን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ አገራትን የሚያቅፍ ነው ፡፡ ንጉሰ ነገስት ጋዳፊ(አገሬው የአፍሪካ ፀሃይ

ይሏቸዋል)  ከዚህ የዲፕሎማሲያዊ ጥረት በተጨማሪ በአፍሪካውያን ንጉሶችና የአገር ሽማግሌዎች በኩል ወደ ታችኛው የህብረተሰብ ክፍል በመድረስ በመንግስታት ላይ ተፅዕኖ ለማድረግ ይሰራሉ ::  ዴይሊ ኔሽን የተባለ የኬንያ ጋዜጣ እንደዘገበው ፕሬዚዳንት ጋዳፊ በፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥረታቸው ዕውን ማድረግ ያልቻሉትን በኢኮኖሚ ተፅዕኖ ማሳካት ይፈልጋሉ::የዓለም አቀፉ የፓን-አፍሪካ ፀሃፊ ታጁዲን አብዱራሂም እንደሚሉት ጋዳፊ ይህን ህልማቸውን ዕውን ለማድረግ በተለያዩ አገሮች ውስጥ በባንክ፣ ሪልስቴት፣ ማዕድን፣ ሆቴሎች ሴክተሮች በመሳተፍ የመንግስታቱን እጅ ለመጠምዘዝ ይሞክራሉ:: ከዚህም በተጨማሪ አፍሪካን ከሌሎች አህጉሮች ጋር ለማስተሳሰር ያስችላሉ የሚባሉ ስብሰባዎችንም በማድረግ የሊቢያን ድምፅ ማጉላት ይፈልጋሉ :: በዚህም ሊቢያ የአፍሪካ-አውሮፓ፣ የአፍሪካ-ላቲን አሜሪካ እንዲሁም የአፍሮ-አረብ ስብሰባን ለማስተናገድ ተንቀሳቅሰዋል:: እየተንቀሳቀሱም ነው :: ይሁን እንጂ የፓንአፍሪካ ዋና ፀሃፊ እንደሚሉት ይህ የሊቢያ ጥረት በምሳሌ መደገፍ ይኖርበታል :: የአፍሪካ ህብረት አድራጊ ፈጣሪ መሆን እንዲሁም የህብረቱ መቀመጫ መሆን ይገባኛል የምትለው ሊቢያ በምሳሌነት ማስተማር ይኖርባታል ::ቢያንስ ድህነትንና አምባገነንነትን ሸሽተው ወደ መሬቷ የገቡ አፍሪካውያንን ማጎርና ማሰቃየት አይገባትም ::

<u>ምን ይደረግ ?</u>

ኒውዮርክም ሆነች ብራስልስ ለንደንም ሆነች ናይሮቢ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ጠብቆ ለማቆየት ብቻም ሳይሆን ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የአጭር መካከለኛና ረጅም ጊዜ ዕቅድ አውጥተው ይንቀሳቀሳሉ :: ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዓለም አቀፉ መድረክ ያላት ገፅታ እየተሻሻለ መጥቷል :: የጠቅላይ ሚኒስትራችንን ጉልህ አስተዋፅዖ ሳንዘነጋ በኔፓድ፣ በቡድን ስምንትና ሃያ፣ በኮፐንሃገን የአየር ንብረት ለውጥ ስብሰባ ላይ የምትደመጥ አገር ሆናለች :: አገራችን የአፍሪካውያን ድምፅ እስከመባል ደርሳለች :: በአፍሪካ ህብረት መድረኮች ላይ የኢትዮጵያ ሚና እየጎለበተ መሆኑን ወዳጅም ጠላትም የሚመሰክረው ሃቅ ሆኗል :: ይህ አንድ ሃብት ነው ::

አፍሪካውያን በዕርስበርስ ጦርነት ሲሞቱ ከሩዋንዳ፣ ብሩንዲ እስከ ዳርፉርና ላይቤሪያ ኢትዮጵያ የንፁሃን ዜጎችን ዕምባ በማበስ አገሮቹ በሁለት እግራቸው እንዲቆሙ

ደግፋለች ። አሁንም እየደገፈች ናት ። በዓለም የሰላም ማስከበር ተግባር ከሚሰሩ አስር አገሮች ውስጥ አንደኛዋ መሆኗን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዜና መዋዕል ይጠቅሳል ። ይህም ሌላ ሃብት ነው ። የኢትዮጵያ አየር መንገድ አፍሪካውያንን እርስ በርሳቸውና ከቀሪው ዓለም ጋር ለማገናኘት እየሰራ ያለው ተግባር ከትርፋማነት ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም ። ዛሬ የብዙ አፍሪካውያን ኩራት ለመሆን የበቃውም ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ወንድሞቿ ያላትን አጋርነት ለማሳየት አየር መንገዱ እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ የሚናቅ አይደለም ።

በአፍሪካ ያለን ተደማጭነት ለማጠናከር እና የድርጅቱን ጽ/ቤት እዚህ ለማቆየት ዋናው ጉዳይ በተለያዩ መስኮች የተጀመሩ የልማት ጥረቶችን ማስቀጠል ነው ። ከሰው በታች ያደረገንን ድህነት ተሸክመን እንኳን በአፍሪካ ይቅርና በአፍሪካ ቀንድም ቢሆን ቀና ብለን መሄድ አንችልም ። ልማት ከሌለ አዲስ አበባን ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተመቸች ማድረግ አይቻልም ። የተሻለ ኢነርጂ፣ የመብራት ኃይል፣ የስልክ፣ የውሃና የመኖሪያ ቤት ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች እንዲኖሩ ሳይደረግ የአፍሪካ ህብረትን መቀመጫ ማቆየት አይታለምም አይታሰብም ። በአገልግሎት አሰጣጥ መስክ የፌዴራል መንግስትም ሆነ የአዲስ አበባ አስተዳደር ዲፕሎማቶችና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚሰሩ ሰዎች ከውጣ ውረድ የሚያድናቸው አሰራር መፍጠር ይኖርባቸዋል ። የቤት ጥያቄ ለሚያቀርቡ ዲፕሎማቶች የምንሰጣቸው የኪራይ ቤቶች ምን ለእነሱ የሚመጥኑ ናቸው ? በአገራችን ብሎም በአዲስ አበባ ያለው የፀጥታ ሁኔታ አስተማማኝነቱ መቀጠል አለበት ። ይህን አስተያየት ስሰጥ የህብረቱን ስብሰባ አዲስ አበባ ስታስተናግድ ህብረተሰቡና የፀጥታ ኃይሎች የመንግስት አካላት የሚያደርጉት የተቀናጀ እንቅስቃሴ በማድነቅ ነው ። የአዲስ አበባን የህብረቱ ዋና ከተማነት ለማረጋገጥ በሁሉም ወገን ዘንድ አንድ የጋራ አመለካከት መፍጠር ይገባል ። በውጭ ግንኙነት ዙሪያ አስተዋፅኦ ያላቸው የመንግስት አካላት፣ ምሁራን፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የንግዱ ማህበረሰብ እና አትሌቶቻችን (ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያን እና ኦሎምፒክን ያጤኗል) ፋይዳውን በተመለከተ ሁሉም የማይተካ ሚና እንዳላቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል ። ገዢውም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህን በመሰለ የብሔራዊ ጥቅም ላይ አንድ አይነት አቋም እንዲያንፀባርቁም እንጠብቃለን ። ሠላም!!